ጌታችሁ ምን እንዳለ ታውቃላችሁን?" ሰሓቦችም "አላህና መልክተኛው ያውቃሉ" አሉ። እርሳቸውም አላህ እንዲህ አለ፦ "ከባሮቼ በኔ ያመነም የካደም ሆኖ ያነጋ አለ

ዘይድ ቢን ኻሊድ አልጁሀኒይ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ ብለዋል፦ የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በሑደይቢያ ምሽት የዘነበን ዝናብ አስከትለው የንጋትን (የሱብሒን) ሰላት አሰገዱን። ሰላቱን ያጠናቀቁ
ጊዜም ወደ ሰዎች በመዞር እንዲህ አሉ "ጌታችሁ ምን እንዳለ ታውቃላችሁን?" ሰሓቦችም "አላህና መልክተኛው ያውቃሉ" አሉ።
እርሳቸውም አላህ እንዲህ አለ፦ "ከባሮቼ በኔ ያመነም የካደም ሆኖ ያነጋ አለ። በአላህ ችሮታና እዝነት ምክንያት ዘነበልን ያለ በኔ ያመነ በከዋክብት የካደ ነው። በእንዲህ እንዲህ የኮኮብ እንቅስቃሴ ምክንያት ዘነበልን ያለ ደግሞ በኔ የካደና በከዋክብት ያመነ
ነው።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በሑደይቢያ (መካ አቅራቢያ የምትገኝ መንደር ናት) የንጋት (የሱቢሕ) ሰላትን በዛ ምሽት ዝናብ ከዘነበ በኋላ አሰገዱ። ሰላቱን በማሰላመት ያጠናቀቁ ጊዜ ፊታቸውን ወደ ሰዎች በመዞር "የተከበረውና የላቀው ጌታችሁ ምን እንዳለ ታውቃላችሁን?" በማለት ጠየቋቸው። ሰሓቦችም አላህና መልክተኛው ያውቃሉ በማለት መለሱላቸው። እርሳቸውም እንዲህ አሉ፦ " ከፍ ያለው አላህ ሰዎች ዝናብ በሚዘንብ ወቅት ለሁለት እንደሚከፈሉ ገለፀ። አንዱ ክፍል በአላህ አማኝ የሆነ ክፍል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአላህ ከሀዲ የሆነ ክፍል ነው።" በአላህ ችሮታና እዝነት ዘነበልን በማለት የዝናብን መውረድ ወደ አላህ ያስጠጋ ሰው ይህ ፈጣሪና የዩንቨርሱ አስተናባሪ በሆነው አላህ ያመነ በከዋክብት ደግሞ የካደ መሆኑን፤ በእንዲህ እንዲህ ኮኮብ ዘነበልን ያለ ደግሞ በአላህ የካደና በከዋክብት ያመነ መሆኑን ገለፀ። ይህ ክህደት የዝናብን መውረድ ወደ ከዋክብት ከማስጠጋቱ አንፃር ትንሹ ኩፍር ነው። ምክንያቱም አላህ በሸሪዐም ሆነ በውሳኔ ዝናብ ለመዝነብ ሰበብ አላደረገውምና ነው። የዝናብን መውረድና ሌሎች ምድራዊ ክስተቶችን ከዋክብት ለመውጣትና ለማረፍ (ለመውደቅ) ወደሚያደርጉት እንቅስቃሴ ያስጠጋና ከዋክብት ትክክለኛ አስተናባሪ መሆናቸውን ያመነ ትልቁን ክህደት የካደ ይሆናል።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/65010